**.ማስጠንቀቅያ/ ጤና**

**እውነታዎች:** በአሁኑ ግዜ  የጤና ጥበቃ ባለሰልጣኖች፡ በአካባቢያችን የኢንፍሉዌንዛ በሽታ እያንሰራራ መሆኑን እየተመለከቱ ነው። ይህም በመሆኑ ከበሽታው ለመከላከል ነዋሪዎች ሊወስድዋቸው ስለሚገቡ እርምጃዎች ዝርዝር አውጥተዋል።  ፓንደሚክ ኢንፍሉዌንዛ (pandemic flu) ሲባል ከአዲስ የኢንፍሉዌንዛ ቫይረስ የሚፈጠር ዓለም አቀፍ ስርጭት ያለው በሽታ ነው። በአጠቃላይ የሰው ልጅ ለአዲስ ዓይነት የኢንፉሉዌንዛ በሽታ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊልም ቢሆን ተፈጥሮአዊ መከላከያ የለውም ። ይህም በመሆኑ ይህ ፓንደሚክ ኢንፍሉዌንዛ ከተራው ኢንፉሉዌንዛ እጅግ ከባድ፡ ብዙ ሰዎችን የሚያጠቃና በየግዜው ከሚታየው ኣንፍሉዌንዛ ይበልጥ ሞት የሚያስከትል ነው።

**ምን ማድረግ ያስፈልጋል፡**

- ጀርሞች/ህዋሳት እንዳይባዙ ማገድ። እጅን በሙቅ ውሃ በደንብ ቶሎቶሎ መታጠብ።
- በሚያስነጥሱበትም ሆነ በሚስሉበት ግዜ ኣፍና ኣፍንጫን መሸፈን፡ መጸዳጃ ወረቀት መጠቀም ወይም ሲያስነጥሱ ወይም ሲስሉ ወደ ላይኛው እጅታዎ መሳል ወይም ማስነጠስ።
- ምግብ፡ የምግብ ዕቃዎችንም ሆነ የፈሳሽ መያዣዎችን  ኣንድ ከሌላው ኣለመዋዋስ።
- በሽታ ከተሰማዎት ቤት ውስጥ ቅሩ። የሚያስነጥሱና የሚስሉ ከሆነ ደግሞ ወደ ሃኪም ይሂዱ፡ሃኪም  የሚሰጥዎትን መመሪያዎችንም ይከታተሉ።
- ኣደጋውን በሚመለከት ኣዲስ መረጃ እንዳለ ለማወቅ በቀጣይነት ሬድዮ ተከታተሉ።
- ***ይህንን መልእክት ለመረዳት፡ ለማየትም ሆነ ለመሰማት የማይችል  የሚያውቁት ሰው ካለ፡ እባክዎትን መልእክትቱ ኣስረዷቸው።***

**ጠቃሚ ዌብሳይቶች:**

http://www.seattle.gov/emergency-management/what-if/hazards/diseasepandemic-influenza

http://www.kingcounty.gov/healthservices/health/preparedness/pandemicflu.aspx